ክፍል ስምንት

፰

# ማጠቃለያና የመፍትሔ ሀሳቦች

## ማጠቃለያዎች

የሚከተሉት ማጠቃለያዎዉች ቅድመ ወሊድ ክብካቤን መሠረት ካደረገው የኤችአይቪ/ኤድስ ቅ ኝት መረጃ ላይ የተገኙ ናቸው:-

- የ1997 ዓ.ም የኤችአይቪ ስርጭት 3.5 ከመቶ ሲሆን በከተማ 10.5 ከመቶ በገጠር 1.9 ከመቶ እንደሆነ ያሳያል፤
- የኤችአይቪ ስርጭት መጠን ከወንዶች ይልቅ በሴቶች ከፍ ያለ ሲሆን በከተማ የሴቶች 4 ከመቶ፣ የወንዶች 3 ከመቶ ነው። ግምታዊው የስርጭት መጠኑም የከተማው ከገጠሩ የሚበልጥ ሲሆን በከተሞች 10.5 ከመቶ እና በገጠሩ ደግሞ 1.9 ከመቶ ነው።
- በኢትዮጵያ በብሔራዊ ደረጃ እና በገጠር አካባቢ የኤችአይቪ ስርጭት መጠን የተረጋጋ ሲሆን በከተማ ስርጭቱ እየቀነሰ መምጣቱን ያሳያል።
- በከተማ ካለው ወረርሽኝ ጋር ሲነፃፀር በገጠር አካባቢዎዉች ያለው የኤችአይቪ ስርጭት በክልሎች እና በቀበሌዎዉች መካከል ያለው የመበላለጥ ደረጃ አነስተኛ ነው።
- በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በአዲስ አበባ እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ያለው የኤችአይቪ/ኤድስ ስርጭት ሁኔታ በሌሎች ክልሎች ካለው ጋር ሲነፃፀር የከፋ ነው። እነዚህ ክልሎች በጥቅሉ በ1997 ዓ.ም. በብሄራዊ ደረጃ በጠቅላላ ከተገመተው የቅኝት ውጤት 86.6 ከመቶ ኤችአይቪ በደማቸው ውስጥ የሚገኝባቸው ሰዎች፤ 86.7 ከመቶ ኤችአይቪ በደማቸው ውስጥ የሚገኝባቸው ነፍሰጡሮች፣ 85.3 ከመቶ አዲስ በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች፣ 87.9 ከመቶ አዲስ የኤድስ ህሙማን እና 88.2 ከመቶ በኤድስ ምክንያት የሚከሰት ሞት ይገኝባቸዋል።
- ኤችአይቪ/ኤድስ በኢትዮጵያ እድገት ላይ ተፅእኖ ማሳደሩን እንደቀጠለ ሲሆን በ1997 ዓ.ም. 1.3 ሚሊዮን ኤችአይቪ በደማቸው ውስጥ የሚገኝባቸው ሰዎች፣ 744,100 በኤድስ ሳቢያ ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናት ሲኖሩ 277,800 ሰዎች ፀረ ኤችአይቪ መድሃኒት ያስፈልጋቸዋል።

- በኢትዮጵያ ኤድስ 34 ከመቶ እድሜያቸው ከ15-49 ለሚደርሱ ሰዎች ሞት ምክንያት ሲሆን በከተማ ደግሞ 66.3 ለሚሆኑት ሞት ምክንያት ሆኗል፡፡

- የፀረ ኤችአይቪ መድሃኒቶች ለሚያስፈልጋቸው ለሁሉም ሲዳረስ በ2002 ዓ.ም. የኤድስ ሞትን ቁጥር በ41 ከመቶ፣ በኤድስ ሳቢያ ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናትን ቁጥር በ13 ከመቶ ሊቀንሰው ይችላል፡፡

## የመፍትሔ ሃሳቦች

በዚህ ዘገባ ከተካተቱት ቅድመ ወሊድ ክብካቤን መሠረት ያደረጉ ብሔራዊ የኤችአይቪ ቅኝቶች እና መርሃ-ግብራዊ መረጃዎች በኢትዮጵያ የኤችአይቪ ስርጭትን ለመቆጣጠር እና የሚያስከትላቸውን ተፅእኖዎች ለመቅረፍ የሚደረጉ ጥረቶችን ለማጠናከር የሚከተሉት እርምጃዉች መወሰድ እንዳለባቸው ያመላክታሉ፡፡

1. ከላይ በተዘረዘሩት መላምቶችና እንዲሁም በሌሎችም ምክንያቶች እና በታየው የወረርሽኙ አዝማሚያ መሀል ሊኖር የሚችለውን የእርስ በእርስ ግንኙነት ለማረጋገጥ ተጨማሪ ጥናት እና ፍተሻ ማድረግ፤

2. ከተሰጠው አጠቃላይ አነስተኛ ስርጭት መጠን በመነሳት ከፍተኛ የመጋለጥ አደጋ ውስጥ ባሉ ቡድኖች በተለይ በከተሞች እና በንፅፅር ከፍተኛ የስርጭት መጠን በታየባቸው ክልሎች እና ስርጭቱ በፀናባቸው የገጠር አካባቢዉዎች የመከላከሉ ጥረት ተጠናክሮ መቀጠል ይገባዋል፡፡ የመከላከል ጥረቱ ከከተማ ወደ ገጠር በሚደረግ ስርጭት ላይ እና በገጠር አካባቢዉዎች የሚታየው ወረርሽኝ ህብረተሰቡን በማንቀሳቀስ አሁን ባለበት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዲገታ ትኩረት ማድረግ አለበት፡፡ ህብረተሰቡን ማንቀሳቀስ እና ማሳተ ፍ በህብረተሰቡ ዘንድ የጉዳዩ ባለቤትነት ስሜት የሚፈጥር ከመሆኑም ባሻገር ህብረተሰቡ የመከላከል፣ የክብካቤ እና የህክምና ግልጋሎቶችን የመጠቀም እድሉ እንዲሰፋ ያደርጋል፤

3. ከተገኘው የቂጥኝ ስርጭት ዘገባ በመነሳት በአገሪቱ በሙሉ በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዉዎች ህክምና የገጠር አካባቢዎዉችንም ጨምሮ አገልግሎት መስጫ ቦታዎዉችን ማጠናከር፤ አመቱን በሙሉ በሁሉም ቅድመ ወሊድ ክብካቤ ክሊኒኮች የቂጥኝ ምርመራ የእለት ተዕለት ተግባር እንዲሆን ማድረግ እና ህክምና እንዲያገኙ ማድረግ፤

4. የወረርሽኙን ስርጭት የሚያፋጥኑ ዋና ምክንያቶች የሆኑ ክፍሎች እና ለኤችአይቪ የሚያጋልጡ አደገኛ ሁኔታዉችን ወይም ከከተማ ወደ ገጠር ለወረርሽኙ መስፋፋት ምክን ያት የሆኑ እና ከፍተኛ ስርጭት ባለባቸው የገጠር አካባቢዉዎች ለኤችአይቪ ስርጭት ምቹ ሁኔታ የፈጠሩትን ለመለየት እና ለመረዳት የሚደረገውን ጥረት በበለጠ ማዳበር የሚያስችሉ ጥናቶችን ማድረግ፤

5. ከፍተኛ የመጋለጥ አደጋ ውስጥ ባሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ ስልታዊ የሆነ የባህርይና ስነ ሕይወታዊ የኤችአይቪ/ኤድስ ቅኝት በተከታታይ ማካሄድ፤

6. 1.32 ሚሊዮን ኤችአይቪ በደማቸው ውስጥ ለሚገኝባቸው ሰዎች እና 744,100 ለሚሆኑ በኤድስ ሳቢያ ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናት ሁለንተናዊ ክብካቤ፣ድጋፍ እና ህክምና እንዲያገኙ ጥረት ማድረግ፣ ከበሽታው ጫና ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ የግብአቶች አቅርቦት እንዲኖር ማድረግ፤ ነፍሰጡር እናቶች የቅድመ-ወሊድ ክብካቤ ግልጋሎቶችን ማግኘት እንዲችሉ ማድረግ፣ የቅድመ-ወሊድ ክብካቤ ግልጋሎቶች ተጠቃሚ ለሆኑ ነፍሰጡር እናቶች የምርመራ እና የምክር አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፣ አገልግሎቱን መስጠት በሚቻልባቸው ተቋማት ቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ ለመከላከል የሶስትዮሽ ህክምና (triple therapy) ማጠናከር፣ ቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የመከላከሉ አገልግሎት በቤት ውስጥ ለሚወልዱ እናቶች እንዲዳረስ ማድረግ፣ ለህፃናት የፀረ ኤችአይቪ ህክምና እንዲሰጥ ማድረግ፣ 50 ከመቶ የሚሆኑት ኤችአይቪ በደማቸው ውስጥ የሚገኝባቸው ሰዎች በገጠር አካባቢ የሚኖሩ በመሆኑ አገልግሎቶቹን ወደ ገጠር ማስፋፋት፤

7. ክብካቤ እና ህክምናን ለማዳረስ እንደ መግቢያ በር የሚያገለግል ስልት በመሆኑ እና የፀረ-ኤችአይቪ ህክምና የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች ለመለየት እና ግልጋሎቱን ለመስጠት ስለሚጠቅም በሳንባ በሽታ(ቲቢ) እና በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች ክሊኒኮች ውስጥ በአገልግሎት ሰጪው አነሳሽነት ላይ የተመሰረተ የምክርና የምርመራ አግልግሎት መስጠትን ጨምሮ ፕሮግራሙንም ይበልጥ ማስፋፋት ያስፈልጋል።

8. የፀረ-ኤችአይቪ ህክምና የሚከታተሉ ተጠቃሚዎች መድሃኒቶቹን ሳያቋርጡ መውሰድ እንዲችሉ የሚያስችሉ ጥረቶችን ማሻሻልን ጨምሮ ግልጋሎቶችን ከማስፋፋት ጋር በተጓዳኝ የእንክብካቤውን ጥራት ደረጃ ማሻሻል እንዲሁም የፀረ ኤችአይቪ መድሃኒቶችን ቫይረሱ ያለውን የመላመድ ወይም የመቋቋም ሁኔታን መከታተል የሚቻልበት የቅኝት ሥርዓት መዘርጋት አለበት።

# ማጣቀሻ


1. ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር። ኤድስ በኢትዮጵያ አምስተኛው ሪፖርት፣ ሰኔ 1995 ዓ.ም.።

2. CSA. The 1994 Population and Housing Census of Ethiopia: Results at Country Level, Vol. 2, Analytical Report, June 1999, Addis Ababa.

3. CSA. Ethiopia Demographic and Health Survey (EDHS) – 2000 and 2005 Reports.

4. Futures Group International. Spectrum Version 2.39 Beta- Policy Modelling System, 2006.

5. HAPCO/MOH. Behavioural Surveillance Survey 2002 and 2005 Reports. Addis Ababa, Ethiopia.

6. MOH. Health and Health Related Indicators 2005. Addis Ababa, Ethiopia.

7. MOH. Accelerating access to HIV/AIDS treatment in Ethiopia, Road map 2004-2006. MOH, Disease Control and Prevention Department, HIV/AIDS and other STDs Prevention and Control Team, 2004.

8. Population Reference Bureau (PRB). World population data sheet. Washington DC. 2000.

9. UNAIDS. 2004. Report on the global HIV/AIDS epidemic, June 2004.

10. UNAIDS. The UNAIDS/WHO Estimation and Projection Package Multigroup Version (EPP Multi) Version 1.0, 2003.

11. Grassly NC et al.(2004). Uncertainty in estimates of HIV/ AIDS: The estimation and application of plausibility bounds. Sexually Transmitted Infections 2004; 80 (suppl.:i31-i38.

በፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
የኤችአይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት
ስልክ፡ ++251-11-5525108 ++251-11-5525702
ፖ.ሣ.ቁ. 122326 አዲስአበባ ኢትዮጵያ